# እውነት መንፈሳዊ ጋዜጣ



# በውስጥ ገጾች

❖ <u>ዕርሰ አንቀጽ፤</u>

በጨለማ ላሉት ብርሃን እየሆንን የህይወት ጣእም ለጠፋባቸው እንደሚያሰማ ጨው ሆነን ለቅዱሳንም መታነጽ ምክንያት በመሆን ክቡር ስሙ በእኛ ከብሮ ዘመናችንን እንፈጽም።

❖ <u>ምስክርነት፤</u>

እናቴ ድንገት እጄላይ ሞተች እህቶቼና ቤተሰብ መላቀስ ጀመሩ እኔ ግን የእናቴ ሞት መቀበል አቃተኝ ሰይጣንን እንዲህ ብዬ አዘዝኩ ሰይጣን ስማ የእናቴን ነፍስ ይዘህ ወደ ሲሆል መውረድ አትችልም በጌታ በኢሱስም መልስ አልኩት ይህንን………

❖ <u>አይኖቻችንን ወደ እግዚአብሔር እናንሳ፤</u>

በሕይወታችን ዘመን ለሆነልንና ለሆነብን ነገር ሁሉ ከፉም ይሁን ደግ ምክንያት ያደረግነው ማንን ነው እያየን ያለነውስ እከሌና እከሊትን ይሆን?

❖ <u>የግጥም መድብል፤</u>

❖ <u>ኢየሱስ ይሻላል፤</u>
እንግዲህ ወገኔ እሳት ከሚነግርህ
ሞት ከሚያስተምርህ
እንግዲህ እንደዛሬው ነገሩ ሳይቀልህ
የምስራቹን ቃል በጊዜ ተቀበል ከልብህ

❖ <u>ማን እንደ እርሱ፤</u>
በሉ ተሰብሰቡ ኑ እንስገድለት
አምልኮና ክብር ምስጋናም ይብዛለት
እልልታ ይሰማ ጭብጨባም አምጡለት
ለሞተልን ጌታ ሁሉም ይገዛለት




በቦስተን የምትገኘው የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ የምታምን የክርስቶስ ኢየሱስን የማዳን ወንጌል ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ የምታሰራጭ ቤተ ክርስቲያን ነች። ይህም ጋዜጣ ወንጌልን ከምታሰራጭባቸው መንገዶች አንዱ ሲሆን በቤተ ክርስቲያኒቱ የሥነ-ጽሁፍ አገልግሎት አባላት እየተዘጋጀ በየሁለት ወር አንድ ጊዜ ይቀርባል።

የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ
ፖስተር ምሕረቱ ሌጂቦ

Email
Meheretu2614@Yahoo.com
Telephone 617-792-5764

**ዋና አዘጋጅ………… ሄኖክ ተሾመ**
**ምክትል አዘጋጅ……..ሐብታሙ አስረስ**
**የውብዳር ፍሰሐ**
**ኮምፒዩተር ዝግጅት ትርሲት ጥላሁን**
**የፊት ገጽ ዲዛይነር……ዝግጅት ክፍሉ**

ለቀጣዩ እትም ይረዳ ዘንድ የእናንተ ተሳትፎ ወሳኝ ሚና ስላለው በሚቀጥለው አድራሻ ያላችሁን አስተያየትና ጥያቄ ላኩልን። **አድራሻችን**

Ethiopian Evangelical Church in Boston
88 Tremont Street
Boston, MA 02108
Email henokekka@yahoo.com
Tel 617 816 8827

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን በቦስተን
88 TREMONT STREET, BOSTON, MA, 02108
T: 617-523-5058 F: 617-523-5058
www.eecBoston.org

# ርዕሰ አንቀጽ

## እንግዶችና መጻተኞች ነን፤

እኛ በበጉ ደም የተዋጀን ቅዱሳን በዚህ ዓለም  ካሉ  ሰዎች ሁሉ የምንለይበት አንዱ ምክንያት በምድር እያለን ሰማያዊውን ኑሮ መጀመራችን ነው።የእግዚአብሔር ቃል ስለ እኛ የሚናገረው መንፈስ ከሆነ ከእግዚአብሔር በክርስቶስ አማካይነት ዳግመኛ በመወለዳችን የእግዚአብሔር ቤተሰብና የሰማይ ሃገር ዜጎች መሆናችንን ነው። ሃገራችን ጌታ ኢየሱስ አሁን ባለበት በላይ በሰማይ ነው። ጌታ ኢየሱስ ራሱ እንዳለው ሥፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና … እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለው ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ ብሎናል። እንግዲህ ሃገራችን በሰማይ መሆኑን ማወቃችን መልካም ነው።ግን ያ ብቻውን በቂ አይደለም ወደ ተዘጋጀልን ሥፍራ እስከምንሄድ ድረስ በዚህ ምድር እንግዶች መሆናችንን አውቀን በእንግድነት ዘመናችን ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን ሰማያዊ ነገር እንጠማ።ወደ ሚጠብቀን ታላቅ ተስፋ ለመግባት በሙሉ ኃይላችን በጽድቅ  ጎዳና እንሩጥ። የቀደሙትን የእምነት አባቶች ፈለግ እንከተል እነርሱ ጌታቸውን በሚገባ አክብረውና አገልግለው የእንግድነት ዘመናቸውን ፈጽመዋል። እኛም ይህች ያለንባት ዓለም መልኳና ክብሯ ጠፊ መሆኑን ሳንዘነጋ ልባችንንና ፈቃዳችንን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለጌታ ፈጽመን በማስገዛት የጌታን የልቡን ፈቃድ አውቀን ልቡ ደስ የሚሰኝበትን ሃሳቡን እንፈጽም። ዘመኑን በትጋት በመዋጀትም በጨለማ ላሉት ብርሃን እየሆንን የህይወት ጣእም ለጠፋባቸው እንደሚያሰማ ጨው ሆነን ለቅዱሳንም መታነጽ ምክንያት እየሆንን ክቡር ስሙ በእኛ ከብሮ ዘመናችንን በክብር እንፈጽመው።

የቤተ ክርስቲያኒቷ መልዕክት



ይህ አምድ የሰዎችን የሕይወት ምስክርነት የምናቀርብበት ሲሆን ለእግዚአብሔር ክብር ለሕዝቡም ደግሞ ጥቅም ይሆናል የምትሉት የሕይወት ምስክርነት ያላችሁ ወገኖች ደውሉልን ወይም ፊትለፊት አግኙን እናስተናግዳለን።

*<u>ምስክርነት</u>*

# አሸንፌብሃለሁ ኢየሱስ

*የዛሬ እንግዳችን መቅደስ አዳሙ ትባላለች ባለ ትዳርና የአንድ ልጅ እናት ስትሆን እግዚአብሔርን የምትወድ እና የምትፈራ በሕይወቷም መልካም ምስክርነት ያላት እህት ነች ከባለቤቷ ከወንድም በላይነህ ጋር የእግዚአብሔርን ቤት በትጋት ያገለግላሉ። ለሕዝብ ጆሮ የደረሰው መዝሙሯ በእውነት እግዚአብሔር በአገልግሎቷ ምን ያህል እንደባረካት ምስክር ነው ይህንን ካሴት ለቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ግዠ እንዲውል በስጦታ መልክ ሰጥታለች በዚህ አጋጣሚ ጌታ ይባርክሽ ማለት እንወዳለን።*



**እህት መቀደስ አዳሙ**

**እውነት… እህት መቅደስ የሕይወት ምስክርነትሽን ለመስጠት ፈቃደኛ በመሆንሽ እጅግ አድርገን እናመሰግንሻለን ጌታ ይባርክሽ ያለሽን የሕይወት ምስክርነት፤ የት እንደተወለድሽ እና እንዳደግሽ፤ ጌታን እንዴት እንደተቀበልሽ፤ በተጨማሪ በልብሽ ያለውን ሁሉብትነግሪን?**

*እህት መቅደስ…. የተወለድኩት ኢትዮጵያ ድሬዳዋ ውስጥ ሲሆን ያደኩት ግን ሐረር ነው አንድ ወንድምና አምስት እህቶች አሉኝ እኔ የቤቱ 3ኛ ልጅ ነኝ አባታችን በልጅነታችን የሞተ ሲሆን እናታችን በጣም ጠንካራና የሥራ ሰው ነበረች የሆቴል ቤት እና የሸቀጥ መደብር ይዛ በሴት አቅሟ ትንቀሳቀስ ነበር ጥሩም የገቢ ምንጭ ነበረን በሆቴል ቤታችን ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ብዙ ሠራተኞች ነበሩ ሁሉም እንደልባቸው በልተው የሚያድሩ ሲሆኑ እናታችን ከእኛም አልፋ ለሌሎች የምትተርፍ ነበረች። ይህ በእንዲህ እንዳለ እናታችን ከልጆቹ ሁሉ ለእኔ ለየት ያለ ፍቅር ነበራት እኔም ለእናቴ እንዲሁ ለየት ያለ ፍቅር ነበረኝ እውነት ለመናገር እጅግ በጣም እንዋደድ ነበር። ከዚህም የተነሳ እኔ በቤት ውስጥ ትልቅ ተደማጭነት ነበረኝ እናቴ አንድ ነገር ማድረግ ብትፈልግ እኔን አማክራ ነው የምታደርገው አይሆንም ካልኩ አይሆንም በቤት ውስጥ ተቀባይነቴ የዚህን ያህል ነበር ሌላው ቀርቶ ስትምል እንኳን በኔ ነው። እኔም በጣም እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ገና በሕጻንነቴ ነው በልቤ ያደረው ከዚህም የተነሳ ሁል ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን አልታጣም ቤተ ክርስቲያኔን (ሃይማኖቴን) በጣም እወዳለሁ። በጣም የሚገርመኝ ገና የ7 ዓመት ልጅ ሆኜ ሰው ወደ መንግስተ ሰማያት የሚገባው እንዴት ነው? እውነተኛው እምነትስ የቱ ው? የሚል ጥያቄ…?ቀጣዩ ወደ ገጽ 6 ዞሯል………!*

# አይኖቻችንን ወደ እግዚአብሔር እናንሳ ፤

በሰው ልጅ የሕይወት ጎዳና ውስጥ ብዙ ውጣ ውረዶች አሉ። ታድያ ሰው ሁሉ ለሚያልፍበት ነገር ደስታም ይሁን መከራ ምክንያት የሚያደርገው ነገር አለው። ምክንያት ያደረግናቸው ነገሮች እኛ ምክንያት አድርገን ሾምናቸው እንጂ እነርሱ በራሳቸው ምንም አይደሉም። ለሆነብንም ይሁን ለሆነልን ነገር ሁሉ የነገሩ ባለቤት እግዚአብሔር ነው ይሉናል የጽሁፉ አቅራቢ።

በሕይወታችን ዘመን ለሆነልንና ለሆነብን ነገር ሁሉ ክፉም ይሁን ደግ ምክንያት ያደረግነው ማንን ነው እያየን ያለውስ እከሌና እከሊትን ይሆን ወይስ ዘመኑን፤ ቦታውን እውቀታችንን እና ጥበባችንን ማንን እያየን ነው ከማንስ እየጠበቅን ነው መጽሐፍ ቅዱስ ሥጋ ለባሽን ትምክህቱ ያደረገ የተረገመ ይሁን ይላል የሰው ልጅ ጠዋት ታይቶ ወድያው እንደሚጠፋ እንፋሎት ነው ያቆ 4፡14፤በዘፍ 25፡22-23 ላይ ያቆብና ኤሣው መንትዬች ነበሩ መገፋፋት የጀመሩት ገና በእናታቸው ማእጸን ሳሉ ነው ይህ ጉዳይ እናታቸው ላይ ጥያቄ ስለፈጠረባት ይህ ለምን ሆነብኝ ስትል ወደ እግዚአብሔር ጮኸች አምላካዊ መልስም በማሕጸንሽ ሁለት ሕዝቦች አሉ እርስ በእርሳቸው አይስማሙም አንዱ ከሌላው የበረታ ይሆናል ታላቁም ለታናሹ ይገዛል አላት ልብ በሉ እግዚአብሔር ይህንን አላማውን ለማስፈጸም እናታቸውን ርብቃን ተጠቀመባት እናት በልጆቿ መካከል አድሎ አደረገች ብኩርናንን በምሥር ወጥ በመግዛት የተጀመረው የበላይነት እሩጫ የሸመገለ አባታቸውን አታሎ በረከት በመቀበል ተጠናቀቀ ታናሹም ሁሉ ይገዛልህ አንተ የበላይ ሁን ተባለለት እንደ ቃሉ ይኸው በዘመናት ሁሉ ታላቅ ለታናሽ በመገዛት ይኖራል በዘመናችን የምናያቸው እስራኤላዊያንና ፍልስጤማዊያን የእነርሱ ውጤቶች ናቸው ይህ የሰው ፈቃድ ያደረገው ነገር አይደለም የእግዚአብሔር ሃሳብ እንጂ የዬሴፍንም ታሪክ ብናየው የሆነው ይኼው ነው ሕልም አየ የሕልሙም ትርጓሜ አስራ አንድ ወንድሞቹ እናት እና አባቱ ጨምሮ ሲሰግዱለት ነው ሆኖም እራዩን ካየበት ጊዜ ጀምሮ ወንድሞቹ ጠላት ሆኑበት ለሞት አሳልፈው ሰጡት ለባርነት ተሸጠ ግብጽ ምድር ገባ ብዙ የመከራ ዘመን አሳለፈ በአሐሰት ተከሶ በወይኒ ተጣለ አስተውሉ ይህ ሁሉ የሰው ሥራ አይደለም የእግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ ይህም ቢሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወት መፈጸሙ ግድ ነበር እና ሰው ሊገምት በማይችለው ታምራት ከእስር ቤት ወይቶ የንጉሥ የቅርብ አማካሪና በሃገሪቱ ላይ ሁለተኛ ሰው ሆኖ ተሾመ ይህ ታዲያ የሰው ሥራ ነው ትላላችሁ ለዮሴፍ መከራው እግዚአብሔር ወዳየለት ግብ መሸጋገሪያ ድልድይ ሆነለት እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።

ውድ የእግዚአብሔር ሰዎች እናንተ ከአምላችሁ ዘንድ ቃል ያላችው ጠላት የቱንም ያህል የበረታ ቢመስልም ውሸት ነው ይልቅ የእርሱ አመጽ እግዚአብሔር ወዳየላችሁ ግብ ያሮጣችኋል ስለዚህ ዛሬ ወደማይለወጠው ታማኝና ጻድቅ ወደ ሆነው ወደነገሥታት ንጉሥ ወደ ጌቶች ጌታ ወደ ታላቁ እግዚአብሔር አይኖቻችንን እናንሳ ያ ስኬትን ይሰጠናል ወደ ከፍታ አውጥቶ የጠላታችንን ከፍታ ያስረግጠናል፤ ባለጋራችንን በጽናት እንዋጋ ድል የኛ ነው በጽድቅ እንኑር እግዚአብሔርን በመፍራት እንራመድ አሸናፊዎች እንሆናለን።

ዘፍ 40፡47 ያሉትን ስምንት ምእራፎች ስታነቡ እግዚአብሔር ለዮሴፍ እንደተናገረው ሆኖለት ታገኛላችሁ ቤተቡ በረሐብ ምክንያት ግብጽ እንደገቡ እንደ ሰገዱለት ተጽፉል እግዚአብሔር አይዋሽም የተናገረውን ይፈጽማል ስለዚህ አይኖቻችንን ከማንም ከምንም ነገሮች ላይ አንስተን ተስፋችን ወደ ሆነው በሰማይና በምድር ሙሉ ስልጣን ወደለው ወደ

እግዚአብሔር እናንሳ ሁላችንን እግዚአብሔር ይርዳን አሜን።

## በእህት ፋንታዬ ወዳጆ

ከገጽ 4 የዞረ…. (ምስክርነት)

ሁል ጊዜ ያብሰለስለኝ ነበር። አስታውሳለሁ አንድ ጊዜ ዶፍ ዝናብ እየዘነበ ከግቢያችን ውስጥ ያለ ግንብ ተደግፌ እግዚአብሔርን እውነተኛውን እምነት እንዲገልጽልኝ እየለመንኩት ያለቀስኩት አረሳውም። ሌላው ገዳምም ለመግባት አስብ ነበር ከዚህም የተነሣ ገዳም እንዴት መግባት እንደሚቻል በልጅ አይምሮዬ እሰልል ነበር በዚህ ሁኔታ ሆኜ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን ልጨርስ አካባቢ ወደ አሥራ ሁለተኛ ክፍል እንደተዘዎወርኩ አሰበ ተፈሪ ሄድኩ። በዚያ ከአያቴ ጋር እየኖርኩ መማር ጀመርኩኝ እንግዲህ እዚጋ ነው ጌታ ኢየሱስ በሕይወቴ ታላቅ ነገር ያደረገው ሁሉ እንዳልተጠበቀው ሆኖ ተቀያየሩ ነገሩ እንዲህ ነው የጓደኛዬ ወንድም ታሞ ልንጠይቀው እቤቱ ሄድን በነገራችን ላይ ይህች ጓደኛዬ ጴንጤ ናት ግን ምንም መስክራልኝ አታውቅም ምክንያቱ ደግሞ በኋላ ላይ ስትነግረኝ ትፈራኝ እንደነበር ነገረችኝ ሆኖም ልጁን ልንጠይቅ በሄድን ጊዜ ሊጸልዩለት ፈልገው አንቺ ሌላ ክፍል ቁጭ በይ አሉኝ በዚህ ጊዜ ሳላውቀው ውስጤ በቁጭት ተሞላ እኔም እጸልያለሁ አልኳት በጣም ደስ አላቸው ማመንም አቃታት ትጸልያለሽ ብለው ጠየቁኝ አዎን አልኳቸው አብሬ መጸለይ ጀመርኩ ልብ በሉ ጴንጤ ግን አይደለሁም እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ስላለኝ ብቻ ነው ታድያ ተንበርክቤ በአንዱ ጆሮዬ ድምጽ እሰማለሁ ቢቃ ጴንጤ ልትሆኚ ነው የሚል በሌላው ደግሞ በሕይወት ዘመንሽ እኮ ለእግዚአብሔር እንዲህ ተንበርክከሽ አታውቂም ይለኛል ድምጽ ነው የምሰማው በዚህ ጊዜ ሊያገለግል የቆመው ወንድም አንቺ እህት ልጸልይልሽ ፈቃደኛ ነሽ አለኝ አዎን አልኩት እጁን ጭኖ ሲጸልይልኝ ድንገት የማላውቀው ኃይል በላዬ ላይ ወረደ ጌታ ኢየሱስን በራይ አየሁት በታለቅ ብርሃ በቃላት ለመግለጽ በሚያዳግት ክብር ቆሞ አየሁት ዘርፋፋ ቀሚስ ለብሷል ፊቱ እንደ ፀሐይ ያበራል ሁሉት እጁን ዘርግቶ ወደ እኔ ነይ ወደኔ ነይ ይለኛል እራሴን ደግሞ ድቅድቅ ያለ ጨለማ ውስጥ ሆኜ እያሳየኝ ይህ ምን ውስጥ እንዳለሁ እሳየኝ መሆኑ ገባኝ በዚህ መልኩ ጌታን አገኘሁ እዛው እንደተንበረከኩ መንፈስ ቅዱስ ተሞላሁ እግዚአብሔር ይመስገን። እርግጠኛ ነኝ በዚህ መልኩ ባይሆን ጌታን አገኛለሁ የሚል ግምት አይኖረኝም ምክንያቱም በጣም አክራ ኦርቶዶክስ ነበርኩ እንደገና ጴንጤ ማለት ለኔ ከሃዲና አታላዬች አድርጌ እቆጥር ነበር። ሆኖም ጌታ በዚህ መልኩ ደረሰልኝ ትምህርቴንም ጨረስኩ በጌታም ጠንክር ብዬ ወደ ቤተሰቦቼ ሐረር ተመለስኩ እንግዲህ እዚህ ጋ ነው የውግያው አይነት የተጀመረው እናቴ በባዕድ አምልኮ ውስጥ ያለች ሴት ናት በቤታችን የባዕድ አምልኮይካሄዳል ሌላው ቀርቶ በቤታችንበሠራተኝነ ወደ ተቀጥረው የሚገቡ በዚሁ በባህድ አምልኮ የተተበተቡ ናቸው። አስታውሳለሁ አንዷ ሠራተኛ በአንድ ክፍል መደብ ተሰርቶላት ዙሪያዋ በጫት ተከቦ ጫት እየቃመች ትጠነቁል ነበር። ታድያ ወደ ቤተሰቦቼ በመጣሁ ጊዜ ጴንጤ መሆኔ ተሰማ እናቴ እጅግ ተቆጣች ጴንጤ ከምትሆን እስላም ብትሆን ይሻለኛል አለች። እህቶቼም በሙሉ ጠሉኝ ነገር ግን አንዷ እህቴ ከኔ ጋር አንድ ክፍል እንኖር ስለነበር እንደመጣው ለሷ መስክሬላት ጌታን ተቀብላለች ሆኖም በየቀኑ ውጊያው እየባሰ መጣ ሰውም ከጴንጤ ጋር እስከመቼ አብረሽ ትኖሪያለሽ ወይ አንቺን ወይ ኢየሱስን ትምረጥ እያሉ ከቤት እንድታስወጣኝ ይጨቀጭቋት ጀመር። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ምግብ በቤት ሰራተኛ እየተሰፈረ ይሰጠኝ ጀመር በእናቴ ቤት እንደ ባዕድ መታየት ሆነብኝ ይህ አልበቃ ብሎ እናቴ አይኔን ማየት ጠላች በእናቴ ዘንድ የነበረኝ ተወዳጅነት በሙሉ ወደ ጥላቻ………..

ቀጣዩ ወደ ገጽ 8 ዞሯል …..

## ማን እንደ እርሱ፤

በዘላለም ፍቅሩ የወደደን
ሕይወቱን የሰጠን ያከበረን
የኃጢያትን እዳ የሻረልን
እረፍት እና ሰላም የሞላብን
በልጁ ታድጎ ልጅ ያደረገን፤
በምሕረቱ ብዛት የሚያኖረን
በመንገዳችንም የሚመራን
ከፍቅሩ ገበታ የሚያጠግበን
በኃጢያት እንዳንወድቅ የታደገን
ከተስፋው እንዳንጎድል የደገፈን
በምንስ ይለካል የፍቅር ጥልቀቱ፤
ከአይምሮ በላይ ነው ስፋት እርዝመቱ
ይሄ ነው አይባል ወርድና ቁመቱ
አይመተር አይገመት በእጅግ ያቅታል
ለኛ ያለው ፍቅር ከመታወቅ ያልፋል፤
በሰማያዊ ጠል ነፍስ ያረሰርሳል
የተጠማ ሁሉ ከእርሱ ይጠግባል
ምህረት ቸርነቱ ለትውልድ ይተርፋል
እንደእርሱ ያለ ወዳጅ ከወዴት ይገኛል
ጠጋ ጠጋ በሉ ኢየሱስ ያዋጣል፤
ከመሬት ያነሳል ከውዳቂ ስፍራ
ጨለማን ያበራል ስሙን ለተጣራ
ፈጣንም መልስ ነው የሕይወት እርካታ
ሰላምና ደስታ የነፍስም እፎይታ
ለዘለአለም ታዟል ከዚህ ታላቅ ጌታ
በሉ ተሰብሰቡ ኑ እንስገድለት
አምልኮና ክብር ምስጋናም ይብዛለት
እልልታም ይሰማ ጭብጨባም አምጡለት
ለሞተልን ጌታ ሁሉም ይገዛለት

በእህት ፀጋ አለማየሁ

## እንታገስ

በአንድ ወቅት አንድ አባት የሦስት ዓመት ልጁን ይዞ በመንገድ ይሄድ ነበር።በሚያልፍበት ጎዳና ላይ በአንድ የአትክልት መሸጫ ሱቅ ውስጥ በጣም የሚያምር ብርቱካን ተቀምጣል ያያል በዚህን ጊዜ ይህንን ለልጄ ልግዛለት ብሎ ጎራ ይላል።ይህ ሁሉ ነገር በአባቱ ልብ ውስጥ ሲጠነሰስ ልጁ ምንም አያውቅም አባቱም ገብቶ በጣም ያማረውን ለልጁ ገዛለት።በጣም የሚገርመው ያ በሰላም ይጓዝ የነበረው ብላቴና ብርቱካኑ ከተገዛበት ደቂቃ ጀምሮ ማልቀስ ይጀምራል አባቱ ምን ሆንክ ቢለው ብርቱካኑን አምጣው አለው።የአባቱ መልስ የገዛሁት ለአንተ ነው ግን አስክልጥልህ ጠብቅ ነበር።ልጅ አሻፈረኝ በሎ መጮሁን ቀጠለ።አባቱ ግን ሊያስረዳው ሞከረ በመጀመሪያ ደረጃ አንተ ይህንን ብርቱካን አላየህውም አላሰብከውም እኔ ግን ላንተ እንደሚጠቅም አስቤ ገዛሁልህ አሁንም መብላት እንድትችል አድርጌ ልላጥልህ እና እሰጥሀለው ልከለክልህ አይደለም ቢለው አሁንም አልሰማ ብሎ ማልቀሱን ቀጠለ።አባቱም ዝም ብሎ መላጡን ቀጠለ ልጁም ማልቀሱን።ታድያ አባቱ ልጦ ሲጨርስ ሰጠው።ቡዙዎቻችን በጌታ ፊት እንዲህ ነን።ነገሮቻችንን ሰርቶ በጊዜው ውብ አድርጎ ሊሰጠን እያዘጋጀልን እየላጠልን ሳለ እኛ ግን ዛሬ ካልሆነ ብለን በብዙ ሐዘንና እንባ እንጮሀለን።ጌታ ነገራችንን ሰርቶ አስኪጨርስ ድረስ እንታገስ!!!

## እንዳንተላለፍ!!!

በእግዚአብሔብር ማዕድ ዙሪያ የምናገለግል ወገኖች የምንሥራው መንፈሳዊ ስራ ነው።ምንም እንደሰው በምድር የምንኖር ቢሆንም ሥራችን ግን ሰማያዊና መንፈሳዊ ነው።መንፈሳዊ ሥራ መንፈሳዊ ምሪት ይጠይቃል።የሥራው ባለቤት ልሁል እግዚአብሔር መንፈስ ነው።የሚያመልኩትም ሆነ የሚያገለግሉት በእውነት እና በመንፈስ ነው።ንጉሥ ዳዊት በዘመኑ ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት የነበረው ሰው

ነበር።በአንድ ወቅት በልቡ እንዲህ አሰበ እኔ በተሸላለሙ ቤቶች ውስጥ እኖራለሁ የእግዚአብሔር ታቦት ግን በድንኳን ውስጥ።ስለዚህ ለእግዚአብሔር ታቦት ማደሪያ እሰራለታለሁ ብሎ በቅን ልብ ቅን ነገር አሰበ።ሃሳቡን አጠገቡ ላለው ለእግዚአብሔር አገልጋይ ለነብዩ ናታን ነገረው።ናታንም በልብህ ያሰብከው መልካም ነው ቀጥል አለው።ልብ በሉ ነብዩ እግዚአብሔርን አልጠየቀም ንጉሥ ዳዊትም የእግዚአ ብሔር ታቦት በድኳን እርሱ ግን በተሸላለሙ ቤቶች መኖሩ አስቆጭቶት ነው ለእግዚአብሔር ታቦት ቤት ሊሰራ የተነሰው።ነገር ግን ልሁል እግዚአብሔር በለሊት ወደ ነብዩ ናታን መጣ።ስማ አለው ደዊት ቤቱን አይሰራልኝም ይልቅ ከጉልበቱ የሚውጣው ልጁ ቤቱን ይሰራልኛል ይህንን ሄደህ ንገርው አለው።ውድ የእግዚአብሔር አገልጋዩች እዚህጋ ሁለት ነገር ልብ እንድንል ያስፈልጋ።

1ኛ እግዚአብሔር ይህንን ሥራ ሊሰራ የሚፈልገው በ ማን ነው? 2ኛ ጊዜው ነው ወይ? እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቅ ብልህነት ነው። እዚህ ጋር ምናልባት በአንዳንድ ሰው ልብ ውስጥ ዳዊት የ እግዚአብሄርን ቤት እንዳይሰራ ሰበብ ሆኖ የተገኘበት ነገር ቢኖር የደም ሰው መሆኑ ነው እኔ ግን ብሎ ስለራሱ.....በዙ እንዲህና እንዲያ ይል ይሆናል ሆኖም ዳዊትን ምሳሌ አደረግነው እንጂ በግልጽ መታወቅ ያለበት ነገር ቢኖር እግዚአብሔር ሁሉን የሚሰራው በራሱ አጀንዳ መሆኑ ነው። ሁላችን ጠንቅቀን ማወቅ ያለብን እኛ የክርስቶስ አካል ነን አካል ሁሉ ደግሞ የየራሱ ስራ አለው አፍንጫ አይን አይን አፍንጫ መሆን እንደማይችል ሁሉ በክርስቶስ አካል ውስጥ ቦታዬ የት ነው እግዚአብሔር በየትኛው ስፍራ እንዳገለግል ይፈልጋል የሚለውን ጠንቅቆ ማወቅ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ላለመተላለፍ በከንቱ ዘመንን ላለመጨረስና ሊሰሩ የተዘጋጁ ሰዎችን ስራ ፊት ከማድረግ ይጠብቀናል። ለእግዚአብሔር መቅናታችን እና መሮጣችን መልካም ነው ነገር ግን እሩጫችን ከንቱ እንዳይሆን ያለ እግዚአብሔር ፈቃድም እሮጠን እንዳናበላሽ ከጌታ ምሪትን ብንቀበል ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር እንዳንተላለፍ ይረዳናል።

በወንድም ሄኖክ ተሾመ

ከገጽ 6 የዞረ (ምስክርነት)

ተቀየረች።እኔ ግን ዕለት ዕለት በጌታ ነገር እየጠነከርኩ መጣው።በአንድ ወቅት እህቶቼን በሙሉ ወደኔ ክፍል ጠርቼ ያማኑሄል አሞጽን ምስክርነት እንዲሰሙ አደረኩኝ ሁሉም በተመስጠ ይሰሙ ነበር። አስታውሳለሁቁጥር አንድ አልቆ ቁጥር ሁለት ሲጀምር ሁሉም በእንባ ነበር የሚሰሙት። በእውነት ልባቸው ተነካ ምስክርነቱን ሰምተው ሲጨርሱ አንድ ጥያቄ አቀረቡልኝ።ይህ ሰው በአሁኑ ሰዓት የምን እምነት ተከታይ ነው?ጴንጤ ነው አልኳቸው።በቃ አንቺ የምትሄጂበት ቤተ/ክርስቲያን ውሰጂን አሉኝ።ጌታ ይመስገን በዚህ መንገድ ጌታ እህቶቼን ምርኮ እድርጎ ሰጠኝ። ወንድሜም ሌላ ቦታ ነበር የሚኖረው በዝያ ስፍራ ጌታን አገኘ እግዝያብሔር የመስገን። ከእናቴ በቀር ሁላችን ጌታን ማምለክ ጀመርን።በዚህ ሁኔታ እያለን አሰበተፈሪ የምትኖረው አያቴ ሞተች። ከዚህ የተነሳ ታላቅ እህቴ የአያቴን ነብረት ልታስተዳድር ወደዝያ ሄደች።ቢሆንም ብዙ መቆየት አልቻለችም ሁኔታውን ለእናቴ ስትነግራት ያለውን ንብረት በሙሉ ጭና እንድትመጣና ቤቱን ግን እንድታከራየው ተነገራት እሷ ግንቤቱን አከራይታ ንብረቱን ጭና ስታበቃ አያቴ ታመልክበት የነበረውን ጨሌ አቃጠለችው ይህ በእናቴ ዘንድ ትልቅ ቁጣ አስነሳብን እናቴም እጅግ ፊት ነሳችኝ እኔም ከቤት ከተባረርኩ ምን ይውጠኛል የሚል ፍርሃት ያዘኝ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለው አንድ ቀን እናቴ እኔ ወደ ምሰራበት ሱቅ በመምጣት ቁልፍ ይዛ ውጣች የክፍሌ በር ላይ ቆማ ጠራችኝ ስደርስ ከቤት ውስጥ የምትፈልጊውን እቃ ካለ አውጭ አለችኝ ለምን? አልኳት ......!

ይቀጥላል ............................. . !